# በመምህርነት ሙያ ላይ ለመሰማራት ከቃዱ ለመጀመሪያዎቹ ሁለት የኮሌጅ ዓመታትዎ ከTREP ጋር በመተባባር እንከፍልሎታለን።

. TREP ምንድን ነው? የመምህራን ምልመላ ትምህርት እና ዝግጅት የአምስተኛ እና ስድስተኛ-አመት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ተማሪዎች ከ12ኛ ክፍል አመታቸው በኋላ ባሉት ሁለት አመታት ውስጥ በኮሌጅ/በዩኒቨርስቲ የትምህርት መስመር የኮሌጅ ዲግሪ እንዲከታተሉ ያስችላቸዋል። የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት ለትምህርት፣ ለሚያስፈልጉ ክፍያዎች እና ለመጽሃፍቶች ይከፍላል።

**አንድ ተማሪ ለ TREP ፕሮግራም ለመቆጠር ብዙ መመዘኛዎችን ማሟላት አለበት።**

1. ተማሪው በ12ተኛ ክፍል ላይ እያለ ቢያንስ አንድ concurrent ኮርስን በተሳካ ሁኔታ ያጠናቀቀ ወይም ለመጨረስ እቅድ ላይ ያለ መሆን አለበት (የሚቀጥለውን ገጽ ይመልከቱ)። በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትዎ የትኞቹ ኮርሶች እንደሚሰጡ ለማየት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማካሪዎን ያነጋግሩ በፎል ወይም በስፕሪንግ ወቅት መመዝገብ ይችላሉ።. ለዚያ ኮርስ መመዝገብ እና የኮሌጅ ክሬዲት ማግኘት አለቦት። ለመመረቅ መንገድ ላይ ያሉ በወደፊት የአስተማሪ ፕሮግራም ውስጥ ያሉ የ12ተኛ ክፍል ተማቲዎች ይህን የኮርስ ስራ መስፈርት በቀጥታ ያሟላሉ።
2. ተማሪው ለኮሌጅ ዝግጁ መሆን አለበት እና በተመዘገበበት ኮርስ መሰረት የማሟያ ኮርስ ስራ አያስፈልገውም። ለኮሌጅ ዝግጁ መስፈርቶች በሚቀጥለው ገጽ ላይ ያለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ።
ተማሪው ከቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤቶች ጋር በመተባበር concurrent enrollmentን በሚያቀርብ ብቁ የሆነ የኮሎራዶ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ ለድህረ ሁለተኛ ደረጃ መርሃ ግብር አመልክቶ ቅበላ አግኝቷል ።
3. ተማሪው የመምህራን ምልመላ ትምህርት እና ዝግጅት (TREP 0 ወደሚባለው ፕሮግራም አመልክቶ ቅበላ አግኝቷል ። ማመልከቻው በየዓመቱ ኖቨምበር 1 አካባቢ ይከፈታል እና ማርች 1 ያበቃል።


*የኮሎራዶ ትምህርት ዲፓርትመንት ከእያንዳንዱ የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ምን ያህል ተማሪዎች በ TREP መሳተፍ እንደሚችሉ እንደሚገድብ ይወቁ። ሁሉም ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች እንዲያመለክቱ እናበረታታለን ነገር ግን በፕሮግራሙ ውስጥ መቀበላቸውን ማረጋገጥ አንችልም።*

**በ TREP ፕሮግራም ውስጥ የትኞቹ የድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይሳተፋሉ?**

ከኦክቶበር 2023 ጀምሮ፣ የሚከተሉት ትምህርት ቤቶች በTREP ይሳተፋሉ፡ አራፓዎ ኮሚኒቲ ኮሌጅ፤ ኮሚኒቲ ኮለጅ ኦፍ አዉሮራ፤ ፣ ኮሚኒቲ ኮሌጅ ኦፍ ደንቨር፤ሬድ ራክስ ኮሚንቲ ኮሌጅ ፣ ሜትሮ ስቴት ዩኒቨርሲቲ /ዴንቨር፣ እና ዩኒቨርሲት ኦፍ ኖርዝርን ኮሎራዶ ዩኒቨርሲቲ።

**በመምህራን ማሰልጠኛ ውስጥ ምን ዓይነት ኮርሶች አሉ?**

ይህ ሰንጠረዥ በኮሎራዶ ዲፓርትመንት ትምህርት የቀረበ ሲሆን በእያንዳንዱ የ CCSD ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚቀርበው ጋር ሊመሳሰሉ ወይም ላይመሳሰሉ የሚችሉ የኮርሶች ቁጥሮችን እና ስሞችን ይጠቀማል። ከእነዚህ ኮርሶች ውስጥ የትኞቹ ኮርሶች concurrent enrollment እንደሆኑ እና የትኛዎቹ ኮርሶች በ12ተኛ ክፍል ለመውሰድ እንደሚገኙ ለማየት ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማካሪዎ ጋር አብረው ይስሩ።




**በወደፊት የአስተማሪ ሙያ ላይ ለመሰማራት ላይ ስለምፈልጉ ተማሪዎችስ ምን ለማለት ይቻላል?** በወደፊት የአስተማሪ ሙያ ላይ ስለምሰማሩት ተማሪዎችስ ምን ለማለት ይቻላል? በ CCSD የወደፊት አስተማሪ ሙያ የተመዘገቡ የ12ተና ክፍል ተማሪዎች የኮርስ ሥራ መስፈርቱን በቀጥታ ያሟላሉ።

**አንድ ተማሪ እንዴት ለኮሌጅ ዝግጁ ነው ተብሎ ይታሰባል/ትታሰባለች ?**

አንድ ተማሪ በፈተና ውጤቶች፣ ኮርሶች ወይም በሁለቱም ጥምር የተገኘ በሂሳብ እና በእንግሊዝኛ ለኮሌጅ ዝግጁ መሆን አለበት።

| **እንግልዝኛ** | **ሀሳብ** |
|---|---|
| SAT English - 470<br>ACT English - 18<br>Accuplacer Next Generation Writing - 246<br>Accuplacer Next Generation AAF - 235<br><br>ENG 1021 – CE English Composition (signed up for concurrent enrollment credit and made C or better) | SAT Math - 500<br>ACT Math - 19<br><br><br><br>MAT 1340 – CE College Algebra (signed up for Concurrent Enrollment credit and made C or better) |

**TREP እንዴት ነው የሚሰራው?**

- ከተማሪዎች ከ12ኛ ክፍል ምርቃቸው በኋላ ባሉት ሁለት የትምህርት ዓመታት የትምህርት፣ መጻሕፍት እና አስፈላጊ ክፍያዎች ይከፈላቸዋል።

- የ TREP ተማሪዎች የትርፍ ጊዜ ተማሪዎች ይሆናሉ (በሴሚስተር 3-11 ክሬዲት ሰዓቶች) ወይም የሙሉ ጊዜ ተማሪዎች (በሴሚስተር 12-16 የክሬዲት ሰዓቶች።)
- The student remains a student in the Cherry Creek School District for two additional academic years folተማሪው ከ12ኛ ክፍል ቀጥሎ ለሁለት ተጨማሪ የትምህርት ዓመታት በቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት ተማሪ ሆኖ ይቆያል. This is called being a 5th year and a 6th year senior. ይህ 5ኛ አመት እና 6ኛ አመት የ12ተኛ ክፍል ተማሪ መሆን ይባላል ምክንያቱም ተማሪው አሁንም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ፣ ተማሪው በ TREP ውስጥ በሚሳተፉበት ጊዜ ለፌዴራል የገንዘብ ድጋፍ እና ለመጪው አዲስ ተማሪዎች የተነደፈ ስኮላርሺፕ ለማግኘት ብቁ አይደለም።
- የኮሎራዶ ኦፖርቹኒቲ ፈንድ (COF) በድህረ ሁለተኛ ደረጃ ተቋም የሚሰጠውን የትምህርት ክፍያ መጠን ይቀንሳል እና CCSD ቀሪውን የትምህርት ወጪ ይከፍላል።
- በTREP የተገኙ ክሬዲቶች እና ውጤቶች ወደ የሁለተኛ ደረጃ ት / ቤት እና እና ወደ የኮሌጅ ትራንስክሪፕት ላይ ይታከላሉ
- ተማሪው/ዋ በኮሌጅ/ዩኒቨርስቲ ኮርስ ይወስዳል/ዳለች። አብዛኛዎቹ ኮርሶች በአካል በመገኘት በኮሌጅ ግቢ ውስጥ መሆን አለባቸው።
- ተማሪዎች የ TREP ዓመታትን ካጠናቀቁ በኋላ የሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማቸውን ከመጨረሻው የ TREP አመት የስፕሪንግ የምረቃ ቀን ላይ ያገኛሉ።
- ተማሪዎች ለመመረቅ መንገድ ላይ ከሆኑ "በማህበራዊ ምረቃ" ላይ እንዲሳተፉ ይበረታታሉ ይህ ማለት በመጀመሪያ ለታቀደለት የምረቃ ዓመት በምረቃ ሥነ-ሥርዓት ላይ በመድረክ ላይ ይራመዳሉ ፡፤ ስማቸውን በምረቃው ፕሮግራም ላይ ይጠራል እና በሁሉም ሌሎች አከባበር የምረቃ ተግባራት ውስጥ ይሳተፋሉ። የመጨረሻውን የ TREP አመት እስኪያጠናቅቁ ድረስ ይፋዊ የሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማቸው ለሁለት አመት ይዘገያል።
- ተማሪው ለአሰሪ፣ ለኢንሹራንስ ወዘተ ሰነዶች ከፈለገ ተማሪው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መልቀቂያ መስፈርቶችን ማሟላቱን የሚገልጽ ደብዳቤ ዲስትሪክቱ ሊሰጥ ይችላል።
- የተማሪው ቤተሰብ በፎል ሴሚስተር በኦንላይን መግቢያ በ my.cherrycreekschools.org ገብተው ምዝገባን ማጠናቀቅ አለበት ነገር ግን ተማሪው ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግቢ መሄድ አያስፈልገውም።

**እንዴት ማመልከት እንደሚቻል**

- ተማሪው/ዋ በመጀመሪያ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማካሪያቸው ጋር ስለ TREP, ለመወያየት፣ ብቁ መሆኑን /ኗን ለማየት እና ስለ ፕሮግራሙ መማር አለበት።
- ተማሪዎች በ12ተኛ ክፍላቸው ከኖቬምበር 1 እስከ ማርች 1 ባለው ጊዜ ውስጥ ማመልከት አለባቸው
- .ተማሪዎች ያገኙትን የኮሌጅ ክሬዲት እንደ የማመልከቻው አካል ለማሳየት <u>መደበኛ ያልሆነ የኮሌጅ ግልባጭ</u> ማቅረብ አለባቸው።
- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማካሪ የሁለተኛ ደረጃ ት / ቤቱን ትራንስክርፕት ያቀርባል.
- ተማሪዎች ወደ TREP ፕሮግራም መገባታቸዉን በሜይ መጨረሻ ላይ ይነገራቸዋል።

- ተማሪው እና ወላጆች በኦንላይን ላይ የASCENT ስምምነትን ይገመግማሉ እና ይፈርማሉ። የ"PandaDoc"የሚባለው የፍርማ ስምምነቶች በተማሪው በተመረጠው ቋንቋ ለተማሪው በCCSD ኢሜይል አድራሻ እና ለወላጅ ቁጥር 1 ኢሜይል አድራሻ ይላካሉ።
- ተማሪ ወደ TREP አመልክቶ ቅበላ ልያገኝ ይችላል ነገር ግን ላለመሳተፍ መወሰን ይችላል። ማመልከቻው አስገዳጅ ስምምነት አይደለም

- አንድ ተማሪ TREP በማንኛውም ጊዜ ከፕሮግራም ለመውጣት ከወሰነ ምንም አይነት የገንዘብ ቅጣት የለም።

ይህ የTREP የማመልከቻ ልንክ ነው።: www.cherrycreekschools.org/page/14839

**ለበለጠ መረጃ**
የተማሪውን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማካሪ ያነጋግሩ
የድህረ ሁለተኛ ደረጃ የስራ ሃይል ዝግጁነት CCSD መምሪያን ያነጋግሩ ታራ ቤል(Tara Bell,) አስተዳዳር, tbell18@cherrycreekschools.org
ማርጋሬት ክሮብ(Margaret Krob), ረዳት mkrob@cherrycreekschools.org
በዲስትሪክታችን ድረ-ገጽ ላይ ያለውን መረጃ ይገምግሙ www.cherrycreekschools.org/page/14839
የኮሎራዶ የትምህርት መምሪያ ድህረ ገጽን
ይገምግሙhttps://www.cde.state.co.us/postsecondary/trepfaqs